ዓለም አቀፍ ትብብር ለኢትዮጵያውያን መብት

**Global Alliance for the Rights of Ethiopians (GARE)**

**PO Box 1836, Rancho Cordova, CA 95741 Telephone: (877) 477-2544**
**www.globalethiopia.org**
**info@globalethiopia.org**

**All Lives Have Equal Value**

በዓለምአቀፍ ትብብር ለኢትዮጵያዊያን መብት (Global Alliance For the Rights of Ethiopians)
የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ
ጥቅምት 2013 ዓ.ም.

ዓለም አቀፍ ትብብር ለኢትዮጵያውያን መብት (ግሎባል አላያንስ) ከልዩ ልዩ አገሮች በተውጣጡና ለአገርና ለወገን ተቆርቋሪ በሆኑ በጎ ፈቃደኛ ኢትዮጵያውያን የተቋቋመውና 11 አባላት ባሉት የባለአደራ ቦርድ የሚመራው ይህ ድርጅት በታዋቂውና በተወዳጁ አርቲስት፡ አክቲቪስት፡ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች፤ የአንድነትና የኢትዮጵያዊነት አቀንቃኝ በአቶ ታማኝ በየነ ሊቀመንበርነት ላለፉት 7 አመታት ካከናወናቸው ተግባራት ዋና ዋናዎቹን፤ ለናሙና ያህል እንደሚከተለው መጥቀስ ይቻላል፡፡

ግሎባል አሊያንስ እ ኤ አ በ2013 በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻችን በአጭር ጊዜ ከአሳዑዲ አረቢያ እንዲወጡ በተገደዱበት ወቅት የደረሰባቸው እንግልትና ሰቆቃ ያስቆጣውን ከአገር ውጭ የሚኖረውን ትውልደ ኢትዮጵያዊ በማስተባበር በመላው አለም በሚገኙ የሳዑዲ ኤምባሲዎች ከፍተኛ ሰላማዊ ሰልፎችን በማድረግ፤ ለሳዑዲ ንጉስ ጠንካራ ደብዳቤ በመጻፍ፤ የኢትዮጵያ መንግስትም ለችግሩ ተገቢ ትኩረት ባለመስጠቱ ጫና በማሳደር 163,000 (አንድ መቶ ስልሳ ሶስት ሺ) ኢትዮጵያውያን በአጭር ጊዜ የአየር ጉዞ ዘመቻ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ከዓለምአቀፍ የስደተኞች ተቋም (IOM) ጋር ተባብሮ ወደየመጡበት አካባቢ የሚመለሱበት መጓጓዣና መጠነኛ የነፍስ ወከፍ ድጋፍ እንዲያገኙ $120,000 ዶላር በመለገስ ስራውን የጀመረ የማኅበረሰባዊ ድርጅት ነው፡፡ በዚሁ ወቅት ከሳዑዲ አረቢያ ወደ የመን ሸሽተው የተደበቁ ወገኖቻችንንም ታድጓል፡፡

**- እ. ኤ. አ. በ2014 ፤**

- ከ20 የሚበልጡ ጋዜጠኞች የሕዝብን ድምጽ መሆናቸው ያስከተለባቸው ወከበና ማሳደድ አስገድዷቸው ወደ ኬንያ ሲሸሹ የገጠማቸውን የኑሮ ችግር ለመቅረፍ ግሎባል አሊያንስ መጠነኛ ድጎማ ተደርጎላቸዋል፡፡

**- እ. ኤ. አ. በ2015 ፤**

- በደቡብ አፍሪካ በሚኖሩ ስደተኛ ኢትዮጵያውያን ላይ የተከፈተውን የጥላቻ ጥቃት ለማስቆም ከፍተኛ የተሟጋችነት እንቅሳቅሴ በማድረግ

**- እ. ኤ. አ. በ2016 ፤**

- በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች አስከፊ ድርቅ ያስከተለው ረሃብ በተከሰበት ወቅት መንግስት ለመደበቅ የሞከረውን በማጋለጥ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፤ የወገኖቻቸውን ሰቆቃ ተገንዝበው የሚችሉትን እንዲለግሱ በማበረታታት፤ እርዳታውም በአስተማማኝ ሁኔታ በተለይ ለህፃናትና ለእናቶች እንዲደርስ ዎርልድ ቪዥን (World Vision) ከተባለው ታዋቂ ዓለምአቀፍ የእርዳታ ድርጅት ጋር የውለታ ሰነድ በመፈራረም $250,000 ዶላር በቀጥታ ለተጎጂዎች እንዲድረስ አድርጓል፡፡
- በሀገራቸው የተንሰራፋውን አፋኝ ስርአትና አስከፊ ድህነት ለመሸሽ ወደ ሊቢያ የተሰደዱ 30 ወገኖቻችን በእምነታቸው ምክንያት በጽንፈኞች ሲታረዱ በውጭ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ መቆጣጠር በሚያስቸግር ጥልቅ የሃዘን ስሜት ተውጦ ሻማ በመብራትና ጸሎት በማድረግ ሲንቀሳቀስ፤ የገንዘብ አስተዋፅዖም እንዲያደርግ በማስተባበር ለእያንዳንዱ የሟች ቤተሰብ በባህላችን መሰረት 10,000 ብር የሃዘንና የመጽናኛ እርዳታ አድርጓል፡፡
- ለሪዮ ኦሎሚፒክ ውድድር ወደ ብራዚል ተጉዘው ከነበሩት አትሌቶች በጊዜው በሕዝቡ ላይ ይፈጸም የነበረውን ሰቆቃ ለዓለም አጋልጠው ውጭ ለመቅረት የወሰኑት ወገኖቻችን ያጋጠማቸውን የኑሮ ችግር ለመቅረፍ ግሎባል አላያንስ የእርዳታ ማሰባሰቢያውን ዘርፍ ሃላፊ ቦታው ድረስ በመላክና ለዕለት ኑሮ የሚያስፈልጋቸውን በማሟላት ወደ ተረጋጋ ሁኔታ እንዲሸጋገሩ አድርጓል፡፡
- ከጉራ ፈርዳ ተፈናቅለው በአማራ ክልል ለተጠለሉ ወገኖቻን የ $25,000 ዶላር እርዳታ ተደርጓል፡፡
- ማላዊ ውስጥ በህገወጥ መንገድ ገብታችኋል ተብለው ከታሰሩ በኋላ ቅጣታቸውን ሲጨርሱ በመጓጓዣ አጦት ሲጉላሉ ለነበሩ ኢትዮጵያዊያን የመጓጓዣ ወጭ መሸፈኛ የ $10,000 ዶላር እርዳታ በመለገስ ወደ ሃገራቸው እንዲመለሱ አድርጓል፡፡

**PO Box 1836, Rancho Cordova, CA 95741 Telephone: (877) 477-2544**
**www.globalethiopia.org**
**info@globalethiopia.org**

**All Lives Have Equal Value**

**- እ. ኤ. አ. በ2017 ፤**

- ለማራቶን አትሌቱ ሙሉጌታ የእርዳታ ማሰባሰብ ዘመቻ አስተባብሯል።
- ከሶማሌ ክልል ለተፈናቀሉ ኦሮምኛ ተናጋሪ ወገኖቻችን የ $25,000 ዶላር አስቸኳይ እርዳታ እንዲደርሳቸው አድርጓል፡፡
- የቆሼ የቆሻሻ ክምር ተደርምሶ በዜጎች ላይ አሰቃቂ አደጋ ባደረሰ ጊዜ ሕይወታቸው ላለፈ ወገኖች ቤተሰብና ከቤታቸው ለተፈናቀሉ ዜጎች የ $13,000 ዶላር እርዳታ አድርጓል፡፡
- በኦጋዴን ተከስቶ የነበረው ድርቅ ባስከተለው ረሀብ ከቀያቸው ተፈናቅለው በመጠለያ ለነበሩ ሶማሊኛ ተናጋሪ ወገኖች በአካባቢው በሚንቀሳቀስ አገር በቀል የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በኩል $15,000 ዶላር አስቸኳይ እርዳታ እንዲደርሳቸው አድርጓል፡፡
- ያለፈቃድ ወደ ሰሜን አሜሪካ ገብታችኋል ተብለው በፍሎሪዳ የኢሜግሬሽን እስር ቤት ይንገላቱ ለነበሩ ኢትዮጵያዊያን ጠበቃ በማቆም እና በአካባቢው ከሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ጋር በመተባበር መብታቸው እንዲከበርና ተለቅቀው ወደ አሜሪካ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡
- የስርአቱ አስከፊነት አስመርሯቸው የተሰደዱ የአየር ሃይል አባላት የገጠማቸውን ጊዜያዊ ችግር ለመቅረፍ የ $11,000 ዶላር እርዳታ ተደርጎላቸዋል፡፡
- በወልቃይት የማንነት ጥያቄ ምክንያት ለተሰደዱ ወጣት ታጋዮች የ $14,657 ዶላር ድጋፍ አድርጓል።

**- እ. ኤ. አ. በ2018 ፤**

- ሀሳባቸውን በሰላም በመግለጻቸው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሰለባ ሆነው ለተሰቃዩ የሕሊና እና የፖለቲካ እስረኞች የ $10,000 ዶላር እርዳታ ተደርጓል።
- በሞያሌ የተከሰተው ብሔር ተኮር ግጭት ሰለባ ሆነው ለተሰደዱ ወገኖቻችን በኬንያ ቀይ መስቀል ማኅበር በኩል የ $10,000 ዶላር እርዳታ ተደርጓል፡፡
- በወልዲያ በቆቦና መርሳ ተፈናቅለው ለነበሩ ወገኖች የ $3,323 ዶላር እንዲሁም በወላይታ፡ ጉራጌ እና ሲዳማ ለተፈናቀሉት የ $18,700 ዶላር ከቤንሻንጉል ጉመዝ ተፈናቅለው ባህር ዳር ላይ ለተጠለሉ ወገኖቻችን የ $10,000 ዶላር እርዳታ እንዲደርሳቸው አድርጓል፡፡
- በደቡብ አፍሪካው የመብትና የነጻነት ትግል አስተባባሪ የነበረው ኢትዮጵያዊ ገዛኸኝ ነብሮ በተገደለ ግዜ ለቤተሰቦቹ ማጽናኛ የሚሆን የ $72,556 ዶላር እርዳታ አሰባስቦ እንዲደርሳቸው አድርጓል፡፡
- በደቡብ ኢትዮጵያ ከመኖሪያቸው ለተፈናቀሉ የወላይታ የጉራጌና የሲዳማ ወገኖች ወቅታዊ እርዳታ አድርሷል፡፡
- በቡራዩ አካባቢ በተፈጠረው ግጭት ሰለባ ሆነው ከመኖሪያቸው ለተፈናቀሉ ወገኖቻችን ከአንድ ወር ባነሰ ግዜ ውስጥ $469,000 ዶላር አሰባስቦ የድርጅቱ መሪ በወቅቱ ኢትዮጵያን ይጎበኙ ስለነበር እርዳታው በትክክል ለተጎጂዎች መድረሱን የሚከታተል ኮሚቴ እንዲቋቋምና ገንዘቡ በልዩ የባንክ ሂሳብ ውስጥ እንዲገባ ተደርጓል፡፡
- ከቤንሻንጉል ጉምዝ ለተፈናቀሉ አማርኛ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያን የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ አድርጓል፡፡
- በራያ የማንነት ጥያቄ ትግል የተገደሉ ታጋዮችን ቤተሰቦች ለማጽናናት መጠነኛ ድጋፍ አድርጓል፡፡
- በለገጣፎ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው በመጠለያ ለነበሩ ተጎጂዎች የ $13,400 ዶላር እርዳታ አድርሷል፡
- በጎንደር አካባቢ ከመኖሪያቸው የተፈናቀሉ ወገኖችን መልሶ ለማቋቋም $100,000 ዶላር እርዳታ አድርሷል፡፡
- በጌድዮ፤ ጎጂ ማንነት ጥቃት ሰለባ ሆነው ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ ዜጎችን መልሶ ለማቋቋም ከወርልድ ቪዥን ጋር በተደረገ ስምምነት ከ $1,114,935 ሚሊዮን ዶላር በላይ አሰባስቦ የተቃጠሉ መኖሪያ ቤቶችን በመስራት ወደ ቀያቸው እንዲመለሱ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ፕሮጀክት በቅርቡ ሙሉ ለሙሉ ተጠናቅቆ በይፋ ይመረቃል፡፡
- በሰሜን ሸዋ የማንነት ጥቃት ሰለባ ሆነው በአጣዬና በከሚሴ አካባቢ ለተጎዱ ኢትዮጵያዊያን ቦታው ድረስ ልዑካን በመላክ የ $16,000 ዶላር ድጋፍ ሰጥቷል፡፡
- ዓለም አቀፍ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በአገራችን ላይ የሚአስከትለውን ጥቃት ለመቋቋም የሚካሄደውን አገር አቀፍ ዘመቻ ለማገዝ ከ $306,301 ዶላር ለጤና ባለሞያዎች የመከላከያ መሳሪያዎችን በአስቸኳይ ከውጭ ገዝቶ በማቅረብ እንዲሁም በጥቁር አንበሳ የአ.አ. ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል፤ በባሕር ዳርና በሃዋሳ ዩኒቨርስቲዎች የሳኒታይዘር ማምረቻ ፋብሪካዎች ለማቋቋም የ $180,000

ዓለም አቀፍ ትብብር ለኢትዮጵያውያን መብት

**Global Alliance for the Rights of Ethiopians (GARE)**

**PO Box 1836, Rancho Cordova, CA 95741 Telephone: (877) 477-2544**
**www.globalethiopia.org**
**info@globalethiopia.org**

**All Lives Have Equal Value**

ዶላር እገዛ በማድረግና ወረርሽኙ በተስፋፋባቸው በልደታና አዲስ ከተማ የአ.አ. ክፍለ ከተሞች ለተጎዱት አቅመ-ደካማ ወገኖቻችን የ $260,000 ዶላር የእለት ኑሮ መደጎሚያ የምግብና የገንዘብ እርዳታ በዎርልድ ቪዥን አማካይነት እንዲደርስ አድርጓል፡፡

- በቅርቡ በኦሮሚያ በደረሰው ዘርና ሀይማኖት ተኮር ጭፍጨፋ በሻሸመኔ ከተማና አካባቢው ቤት ንብረታቸው ለወደመባቸው ተጠቂዎች የ $130,000 ዶላር እርዳታ በወርልድ ቪዥን አማካይነት እንዲደርስ አድርጓል፡፡
- በሊባኖስ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ከስራቸው ተፈናቅለው በመንገድ ላይ በመውደቃቸው ቤት ተከራይቶ እንዲጠለሉ ከማድረጉም በላይ በጣም ችግረኛ ለሆኑት ወደ አገራቸው የሚመለሱበትን የመጓጓዣ ድጋፍ በመስጠት በመታድግ ላይ ይገኛል።
- በቅርቡ በአፋር በተከሰተው የጎርፍ አደጋ የተጎዱ ወገኖቻችንን ለመታደግ ከኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር ጋር በመተባበር ከ $30,000 ዶላር በላይ የሚያወጣ አስቸኳይ የምግብ እርዳታ እንዲደርሳቸው አድርጓል፡፡

ይህንን ሁሉ ለማከናወን ቀደም ሲል በነበረው የአፈና ስርአት ውስጥ ከመንግስት እይታ በመደበቅ ተባባሪዎቻችንን ለእስርና እንግልት ላለማጋለጥ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግና በርካታ ተግዳሮችን መቋቋም ነበረበት፡፡ ይህንንም በማሳካት መስዋዕትነት የከፍሉትን ሃገር ወዳድ ተባባሪዎቻችንን ሁሉ ማመስገን እንወዳለን፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ሁሉ ማድረግ የተቻለው ከአገር ውጭ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ለወገኑ ባለው ከፍተኛ ተቆርቋሪነትና ልገሳ፤ በግሎባል አሊያንስም ግልጽ አሰራርና ጠንካራ አመራር ባተረፈለት ተዓማኒነት በመሆኑ በዚህ የወገን-አድን በጎ አድራጎት ስራ ለተሳተፉት ሁሉ ጥልቅ የሆነ ልባዊ ምስጋና እናቀርባለን፡፡

ከሁለት ዓመታት በፊት የድርጅቱ አመራሮች ልዑካን ኢትዮጵያን በመጎብኘት ከከፍተኛ የመንግስት የስራ ሀላፊዎች እና ሙብት ተኮር ከሆኑ ማህበረሰባዊ ድርጅቶች መሪዎች ጋር በመገናኘት ግሎባል አሊያንስ ኢትዮጵያን ወደ እውነተኛ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የማሸጋገሩን ሂደት በሚያግዝ መልኩ በአገር ውስጥ ስራውን ማካሄድ በሚችልባቸው ሁኔታዎችና የእርዳታ አድማሱንም አሥፍቶ አስካሁን ከሚያደርገው የገንዘብ፤ የቁሳቁስ፡ የሕግና የሞራል እርዳታዎች በተጨማሪ በውጪ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ከፍተኛ እውቀትና ክህሎት የአገር ግንባታውን እንቅስቃሴ ለማሳካት ተገቢውን ዘላቂ አስተዋጽኦ ማድረግ እንዲችል ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ጥናታዊ ዝግጅት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ለዚህም እንዲያግዝ አንድ የተለያዩ አካላትን የሚወክልና በጎ ፈቃደኞችን ያካተተ ጠንካራ የግሎባል አላያንስ የድጋፍ ቡድን በኢትዮጵያ ተቋቁሞ ከፍተኛ እንቅሳቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል። ወደፊትም በሚቀረፀው ፍኖተ ካርታ መሰረት ግሎባል አላያንስ በሀገር ውስጥ የሚዘረጋው መርሃ-ግብር በቅርቡ ለሕዝብ ይፋ ይደረጋል፡፡ በዚያም ወቅት የሚያደርገው ጥረት ሁሉ ለሃገርና ለወገን አለኝታነቱን በተግባር ለማስመስከር መሆኑን ተገንዝቦ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በፈቃደኝነት የዚህ ግብረ-ሰናይና የሙብት ተሟጋች እንቅስቃሴ ደጋፊ በመሆንና የሚችለውን እርዳታ በማድረግ እንዲተባበር ወገናዊ ጥሪ እናቀርባለን፡፡

እስካሁንም በሀገር ውስጥ ከመንግስት እና ከማህበረሰባዊ ድርጅቶች ሃላፊዎች ለተደረገለት ትብብርና ድጋፍ ምስጋና ማቅረብ እንወዳለን። በሃገር ውስጥ ግሎባልን በመደገፍ የሚንቀሳቀስ ቡድን አባላት ከፍተኛ መስዋዕትነት እየከፈሉ ሌት ተቀን ለወገን ደራሽነቱን በማስመስከራቸው የላቀና የተለየ ምስጋናና ክብር ይገባቸዋል፡፡

ኢትዮጵያ በዜጎቿ ጥረትና ትብብር ከችግር ተላቅቃ የሰላም የዲሞክራሲ የብልጽግና አገር ትሆናለች !!